የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
**ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)**

አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ

# በኦሮሚያ ክልል የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችንና በአዲስ አበባና ዙሪያው ያሉ የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴዎችንና አስመልክቶ ከኢሰመጉ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የካቲት 15/2015 ዓ.ም

## ከቤት ፈረሳ ጋር ተያይዞ የተስተዋሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በአዲስ አበባ ከተማ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ሰፋ ያለ የቤት ፈረሳ እየተካሄደ መሆኑን እና ኢሰመጉም በቅርበት ጉዳዩን እየተከታተለ ሲሆን ከእዚህም ጋር ተያይዞ ለምርመራ የሄዱ የኢሰመጉ አራት የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም መታሰራቸው ይታወሳል። ይህ ቤት የማፍረስ እንቅስቃሴ አሁንም በስፋት የቀጠለ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ሰበታ፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ ለገዳዲ፣ ሱሉልታ፣ ኤር ሞጆ፣ ገላን እንዲሁም ሌሎች አካባቢዎች በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክፍለ ከተማና ቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ቤት ፈረሳዎች ተካሂደዋል። ከእዚህም ድርጊት ጋር ተያይዞ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳቶች መድረሳቸውን በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በጸጥታ ሀይሎች እና ቤቶቻቸው በሚፈርሱባቸው ሰዎች መካከል ውጥረቶች መፈጠራቸውን እንዲሁም ከእዚህ ድርጊት ጋር ተያይዞ እስራቶች መፈጸማቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል። ህገወጥ የቤት ግንባታ የሚበረታታ ድርጊት ባይሆንም በእነዚህ አካባቢዎች ላይ የሚደረጉ ፈረሳዎች የቤት ግንባታዎቹ ሳይጀመሩ በፊት ማስቆም የተሻለ የነበረ ቢሆንም ብዙ ሃብት ከፈሰሰበት በኋላ እንዲሁም ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ባሉበት በተጨማሪም ምትክ ስፍራ ወይም ጊዜያዊ ማቆያ ስፍራ ሳይዘጋጅ ቤታቸው መፍረሱ ተገቢነት የሌለው መሆኑ እንዲሁም አንዳንዶቹ ፈረሳዎች የህግ ስነ-ስርዓትን ያልተከተሉ፣ ከመንግስት በኩል ተመጣጣኝ ያልሆነ የሀይል እርምጃ የታከለባቸው፣ ህጋዊ ቤቶችም ጭምር የፈረሱበት፣ አንዳንድ ቤቶች ደግሞ የመብራት እና የውሀ አገልግሎት የመንግስት ተቋማት ያስገቡላቸው እና ይህ በሚደረግበት ወቅት ምንም አይነት የህጋዊነት ጥያቄ ያልተነሳባቸው፣ አንዳንዶቹ የፈረሱ ቤቶች ከተሰሩ 15-20 አመታትን ያሳለፉ መሆናቸው እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች የፈረሳ ድርጊቱ ህጋዊነት ላይ ጥያቄን እያስነሱ እንደሚገኙ ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል።

## በኦሮሚያ ክልል እየተፈጸሙ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

በኦሮምያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ቄለምና ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በመንግስት፣ በሸኔ እና ሌሎች ታጣቂ ኃይሎች መካከል በሚደረጉ ግጭቶችና በኃይል በሚያዙ አካባቢዎች የመንግስትን የጸጥታ አካላትንና የታጣቂ ቡድኑን አባላት ጨምሮ በርካታ ንጹሃን ዜጎች ላይ የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት፣ ህገ ወጥ እስር እና አፈና እየደረሰ እንደሚገኝ እንዲሁም ንጹሃን ዜጎች ከሚኖሩበት ቤት፣ ከመንገድ ላይ እና ከሚሰሩበት ቦታ በመንግስት የጸጥታ አካላት በሃይል ተወስደው እየታሰሩ እንደሆነና አንዳንዶች በሃይል ተይዘው ከተወሰዱ በኋላ የት እንዳሉ ቤተሰቦቻቸዉና ዘመዶቻቸዉ ባለማወቃቸው የተ ጎጂ ቤተሰቦች በችግር ውስጥ መሆናቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለማወቅ ችሏል። ይህ ድርጊት አሁንም ድረስ እንደቀጠለ በመሆኑ ዜጎች ንብረታቸው እንዲወድምና ቤት አልባ እንዲሆኑ፣ ህይወታቸውን እንዲያጡ፣ አካላቸው እንዲጎል፣ ያለጥፋታቸው እንዲታሰሩ ምክንያት በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መሆናቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል። በኦሮሚያ ክልል በመንግስት የጸጥታ አካላት፣ በሸኔ እና ሌሎች ታጣቂ ኃይሎች መካከል በሚደረጉ ውጊያዎች ምክንያት ዘርፈ ብዙ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በዋናነት ከላይ በተጠቀሱት አራት የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከመንግስት በኩል ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ ምክንያት፣ ታጣቂ ቡድኑ በተደጋጋሚ በሚፈጽማቸው ጥቃቶች እንዲሁም የመንግስት የጸጥታ አካላት የመለ የት መርህን ወደጎን በመተው በንጹሃን ላይ በሚወስዱት እርምጃ ጭምር በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመውባቸዋል። ይህ ጉዳይ ከመንግስት በኩል ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ ምክንያት የችግሩ አሳሳቢነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ አድርጎታል።

## ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡

የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ አንቀጽ 25(1) ማንም ሰው ለእራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደኅንነት በቂ በሚሆን የኑሮ ደረጃ የመኖር መብት እንዳለው እና ይህም መብት መጠለያን እንደሚጨምር ይደነግጋል። የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ

መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 11 ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ በሆነ የኑሮ ደረጃ የመኖር መብት እንዳለው ይደነግጋል። በቂ የሆነ መጠለያ የማግኘት መብት በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ ከመኖር መብት የመነጨ ሲሆን ሌሎቹን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ለመጠቀም ዋነኛ ጠቀሜታ እንዳለው የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮሚሽን ጠቅላላ አስተያየት ቁጥር አራት ይገልጻል። ሰዎችን ከመኖሪያ ቤትና ከመሬት አስገድዶ ከማፈናቀል (Forced Eviction) የመቆጠብ እና በሌሎች እንዳ ይፈናቀሉ የመከላከል የመንግስት ኃላፊነት የመነጨው በቂ መጠለያ ከማግኘት የሰብዓዊ መብት እና ከሌሎች ሰብዓዊ መብቶች መሆኑን የተባበሩት መንግስታት በበቂ መጠለያ መብት ላይ ልዩ ዘጋቢ ባወጣው ዘገባ ይገልጻል። የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40 (7) ላይ ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 8 ላይ ደግሞ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል ሲል ይደነግጋል።

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ (ICCPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል። የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 “ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው” ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማነም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል። በእነዚህ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ህጎች ላይ የመንግስት ዋነኛ ኃላፊነት የዜጎችን መብት የማክበር፣ የማስከበር እና የሟሟላት እንደሆነ ይታወቃል። ነገር ግን የመንግስት የጸጥታ አካላት ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ከዳኝነት ውጪ የሆነ ግድያ ሲፈጽሙ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያሳይ እና በወንጀል ተጠያቂ ሊያስደርግ የሚገባው ነው።

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- በአዲስ አበባ ከተማና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ በሚገኙ አካባቢዎች እየተከናወኑ ያሉ የቤት ፈረሳዎች ተገቢውን የህግ ስነ-ስርዓት የተከተሉ እንዲሆኑ እና በምንም አይነት ከቤትና ከመሬት አስገድዶ የማፈናቀል (Forced Eviction) ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ፣
- መንግስት የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴዎችን በሚያደርግበት ወቅት ህጋዊ የሆኑ ቤቶችን ከማፍረስ እንዲቆጠብ እንዲሁም ህጋዊ አይደሉም የሚባሉ ቤቶችም ቢሆኑ ቤት መስራት በሚጀመርበት ወቅት ማስቆም የሚቻልበት ሁኔታ ማመቻቸት እንጂ ለረጅም ዘመን ኑሮን መምራት ከጀመሩ በኋላ የሚደረጉ ፈረሳዎች ሰብዓዊነትን ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ በመሆኑ እንቅስቃሴው ተገቢ ትኩረት ቢሰጠው እንዲሁም የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴው ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ወቅት ለሚፈርሱ ቤቶች ተገቢውን ካሳ እንዲሰጥ፣
- በቤት ፈረሳዎች ወቅት የሚስተዋሉ ከመንግስት በኩል ተመጣጣኝ ያልሆኑ የሀይል አጠቃቀሞች በአስቸኳይ እንዲቆሙ
- ከቤት ፈረሳ እንቅስቃሴዎቹ ጋር ተያይዞ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ቤቶች በሚፈርሱበት ወቅት ለነዋሪዎች በቂ ጊዜ በመስጠት ቅድሚያ እንዲያሳውቁ እንዲሁም ንብረታቸውን ለማውጣት በቂ ጊዜ እንዲሰጡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለወደሙ ንብረቶች ግን መንግስት ተገቢውን ካሳ እንዲሰጥ እንዲሁም ይህንን ህገ-ወጥ ድርጊት የሚፈጽሙ አካላትን በህግ እንዲጠይቅ፣
- በተቻለ መጠን የቤት ፈረሳ እንቅስቃሴው ህዝብን ተጠቃሚ ማድረግ ዋነኛ አላማው ከሆነ ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት በአካባቢ ላይ የሚኖሩ እና ቤቶቻቸው የሚፈርስባቸውን ሰዎች ጋር ውይይት በማድረግ አካታች የሆነ ዘላቂ መፍትሄን ማምጣት እንዲቻል፣
- በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ቄለምና ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞኖች ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ በመንግስት የጸጥታ አካላት፣ በሸኔ እና ሌሎች ታጣቂዎችና መካከል በሚደረጉ ውጊያዎች ምክንያት የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ እንዲሁም ሁለቱም አካላት ንጹሀን ሰዎችን ኢላማ ከማድረግ እንዲቆጠቡ፣
- የኦሮሚያ ክልል መንግስት እንዲሁም የፌደራል መንግስት በኦሮሚያ ክልል፣ በሸኔ እና ሌሎች ታጣቂዎች ጋር የሚደረገውን ውጊያ ተከትሎ ለሚፈናቀሉ ሰዎች ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ እንዲሁም ለተፈናቃዮች አስፈላጊውን ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያቀርቡ፣
- የኦሮሚያ ክልል ለሸኔ ታጣቂ ቡድን ያቀረበው የሰላም ጥሪ እንደከዚቀደሞቹ ለቡድኑ የቀረቡ ነገር ግን ሳይሳኩ የቀሩ የሰላም ጥሪዎች እንዳይሆን ሁለቱም አካላት አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ፣
- ኢሰመጉ የመዘዋወር ነጻነት ጋር ተያይዞ የካቲት 09 ቀን 2015 ዓ.ም መግለጫ በማውጣት የሰዎች የመዘዋወር ነጻነት እንዲከር ጥሪ ያደረገ ቢሆንም ይህ ድርጊት አሁንም መታረም ያልቻለና የቀጠለ ሲሆን ጎህጺዮን አካባቢ መንገደኞች ወደ አዲስ አበባ መግባት አትችሉም እየተባሉ እየተመለሱ በመሆኑ የሚመለከተው የመንግስት አካል ለእዚህ ድርጊት ዘላቂ እልባት እንዲሰጠው፣

- ሲቪል ማህበራት፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ ሚዲያዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው አከላት በኦሮሚያ ክልል በመንግስት የጸጥታ አካላት በሸኔ እና ሌሎች ታጣቂዎች የሚደረገው ውጊያ አንዲቆም እንዲሁም የሰላም ጥሪው እንዲሳካ የበኩላቸወን በጎ አስተዋጾ እንዲያደርጉ እንዲሁም መንግስት በአካባቢ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እንዲያቆም፣ እንዲያስቆም እና ግጭቱን ተከትሎ ለተፈናቀሉ ሰዎች ተገቢውን ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያደርግ እንዲወተውቱ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ